# ሳያጣሩ ወሬ ሳይገድሉ ጎፈሬ

በአቶሰውየው ከሰሜን አሜሪካ

ይድረስ ለአቶ አበበ በለው
የአዲስ ድምፅ ራዲዮ አዘጋጅ
ዋሺንግተን ዲሲ

ያገሬ ሰው ሲተርት "የአፍ ወለምታ በቂቤ አይታሽም" ይላል። ያም ምንም ማስረጃ በሌለን ያልተጣራ ወሬ ይዘን እንዳንርገ ለማሳሰብ መሰለኝ። በተለየ በዘመናዊው ዓለም የዘመናዊ መገናኛ ባለቤትነትና (ራዲዮ) አሰራጭነት ጋር አብሮ ተጠያቂነትም እንዳለ እኔ ላንተ ላስረዳ ብዬ ብል ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች ይሆንብኛል።

በትላንትናው ዕለት (ማለትም ቅዳሜ ነኀሴ 11 ቀን 2005) ኢሕአፓን በሚመለከት ያቀረብከውን የቃለ መጠይቅ ዝግጅት በጥሞና ተከታትያለሁ (ዝጅቱን ለመከታተል ለምትሹ እነሆ፡- Radio Show For August,17,2013 http://www.addisdimts.com/?p=10232 ያድምጡ)። ባስተላለፍከው ቃለ መጠቅ ላይ ካቀረብካቸው እንግዶች አንዱን ኢሕአፓ ጸ/ቤት በምትደውልበት ጊዜ የምታገኘው መሪ መሆኑን ስትናገር ሰምቼ ማመን አቅቶኝ አዝኛለሁ። እንግዲህ የአዞ እንባ ካልሆነ በስተቀርና በእርግጥም የምትፈልገው የኢሕአፓን መጠንከር ከሆነ ኢሕአፓን በሚመለከት የምታቀርባቸው ዝግጅቶች ዕውነታ ላይ የተመሠረቱ እንዲሆን ማድረግ የሚጠበቅብህ የሙያህ ሃላፊነት እንደሆነ ላስገነዝብህ እወዳለሁ።

ኢሕአፓን የመሳሰሉ አጀንዳቸው ኢትዮጵያዊነት የሆኑ ድርጅቶች ወደድንም ጠላንም በተቀነባበረ ሁኔታ ውጥረት ውስጥ እንዲገቡ የማያቋርጥ ዘመቻ በተለያዩ የኢትዮጵያ ጠላቶች እንደሚካሄድባቸው ሁሉም አደባባይ ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ነው። በተለይም ኢሕአፓ ከውስጥም ሆነ ከውጪ የሚሰነዘርበትን የአፍራሽ እንቅስቃሴ ለይተው የሚመዝኑበት የብዙ ዓመታት ተመክሮን ያካበቱ አባላትና ደጋፊዎች ያሉት ነው። ስለሆነም ያቀረብከው ዝግጅት ላይ አቶ ዘርጋው እንደ ድርጅቱ መሪ ያስተላለፍከው የተሳሳተ መልዕክት በቅርብህ ከሚገኘው የድርጅቱ ጽ/ቤት በማረጋገጥ ዕርማት ብታደርግ የሚያስከብርህና ዕውነታውን ሕብረተሰቡ እንዲያውቅ ጥረት ለማድረግህ የምታረጋግጥበት ነው እላለሁ። በእርግጥም ካቀረብካቸው ወገኖች አቶ ዘርጋም ቢሆን እንደ ኢሕአፓ መሪ ስታቀርበው የማስተባበያ ቃል አለመተንፈሱ (በቃለ መጠይቁ ጊዜ ዕድሉም እያለው) እንግዲህ እንደኔ ያለው ቆምኩበት የሚለው "የእርማት እንቅስቃሴን" መሠረት እንድጠይቅ ያደርገኛል።

ስላቀረብካቸው እንግዶች በዚህ ጽሑፌ የምሰጠው አስተያየት ባይኖርም፣ አንተንም ወንድሜን የማሳስብህ ዕውነተኛውን ለማግኘትና ለመዳሰስ ሁሉኑም ወገን ማድመጡና ማጣራቱ ይረዳሃል ብዬ እገምታለሁ። ካለበለዚያ ግን "ሳያጣሩ ወሬ ሳይገድሉ ጎፈሬ" እንዳይሆንብህ እፈራልሃለሁ።

ከአክብሮት ጋር

አቶሰውየው (ከሰሜን አሜሪካ)